የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
# የ2011 በጀት ዓመት የ4 ወራት ሂሣብ
# ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት /2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

## የ2011 በጀት ዓመት  የ4 ወራት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከመጋቢት 1/2011 እስከ ሰኔ 30/2011 ዓ.ም የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚንስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ሚንስቴር መ/ቤቱ ያቀረባቸው ሪፖርቶች መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች

ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

**ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣**

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ገቢ፤**

1. በድምሩ ብር 10,337,208.97 የገቢ ደረሰኝ ባለመቅረቡ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም::

**ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

2 በድምሩ ብር 2,628,466.48 ማስረጃዎቹ ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የቆይታ ግዜውንና የተሰብሳቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም::

**ተከፋይ ሂሳብ፤**

3 በሂሳብ መደብ 6174299/ 5004/ ልዩ ልዩ ተቀማጭ/ ብር 304,040,538.89 ማስረጃው ባለመቅረቡ የተከፋይ ሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም::

**በጀት፤**

4. የመደበኛ በጀት ብር 1,694,825.08 ከተደለደለው በላይ ወጪ መደረጉ ታውቋል::

2

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 በተገለጹት ሁኔታዎች መሠረታዊነትና ጉልህነት የተነሳ የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በትክክል ያሳያሉ ብሎ አስተያየት መስጠት አልተቻለም፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣**

5. የመደበኛ በጀት ብር 70,739,679.76 ሥራ ላይ ያልዋለ ተገኝቷል፡፡

ከሰላምታ ጋር

------------------------

ትዕግስት ሬዎ
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር